# ተማሪም ሙስሊምም መሆን አይቻልምን?

## (ነፃ አስተያየት)

**ከአብዱራህማን አደም**

የሙስሊሞች የህልውና ጉዳይ የሆነው ሰላትን በኢስላማዊ አኳኋን (በጀመዓ-በጋራ) መስገድ ዛሬ በተከለከለበት ትግራይ በኩል የነበር የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች (ሰሀቦች) በሐይማኖታቸው የሚደርስባቸውን ግፍና መከራ ሸሽት ወደ ኢትዮጵያ የተሰደዱት:: ያኔ ነው የኢስላምና የኢትዮጵያ ግንኙነት ገና ከመጀመሪያው ምዕራፍ ሀ ብሎ የተጀመረው:: አርቆ አሳቢ፤ አስተዋይ እና ፍትሃዊ መሪ ነጃሲ የተባለ መሪ ስለነበር ሁሉም ነገር በግሩም መልክ ተጓዘ:: ክርስቲያን መሆኑ በሙስሊሞች ላይ የተለየ አመለካከት እንዲኖረው አላደረገውም:: ይሁን እንጂ ያ ታላቅ የኢትዮጵያ መሪ የነበረው ነጃሲ ከ14 ክፍለ ዘመናት በፊት የነበረው አይነት ቅን አሳቢነት ዛሬ በ21ኛው ክፍለ ዘመን በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ሲጎድል ይስተዋላል:: ለዓለም ተምሳሌት የሚያደርገው ያ አኩሪ ታሪክ በተመዘገበበት ምድር «ተማሪም ሙስሊምም መሆን አይቻልም» የሚሉ በጥላቻ የተሞሉ ግለሰቦችን ያፍራ? አይ! ነጃሺ ልጅ አልወጣለትም! ከማለት ሌላ ምን እንበል?

አምባገነኑ የአፄው ሥርዓት ተፈንግሎ ቢጣልም የነርሱ ርዝራዦች የሉም ማለት እንችላለን? ተመልሶ እንደማይመጣም ማንስ እርግጠኛ መሆን ይችላል? አላህ ብቻ ነው የሩቀን አዋቂ:: ፀረ-ኢስላም አቋም በነበረው በአፄው ሥርዓት ሙስሊሞች በሀገራቸው እንዳይኮሩ ተደርገዋል:: ተወልደው እትብታቸው በተቀበረበት ሀገር መጤ ተባሉ:: የመማር መብት ተነፈጉ:: ሴራ ተጠንስሶ ከትምህርት ቤት ደጃፍ እንዳይደርሱ ተደረጉ::

የሴራው አይነት እንደየዘመኑ ለየቅል ነው:: ለአብነት ያህል ብናይ በአፄ ሐይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት በሙስሊሙ ላይ ጥናት ተደርጎ እንዳይማር በዘዴ እቀባ ተደረገበት:: «ሙስሊሙ ለምን እንዲማር አይደረግም?» ብሎ መጠየቅ አይቻልም ነበር:: ለምን ቢሉ ኢትዮጵያዊስ መች ሆኑና! በአንድ ወቅት ጋዜጠኛ የነበሩት ሀጅ በሺር ዳውድ ይህንን ጥያቄ አንድ የወቅቱን ገዢ የነበሩትን ግለሰብ ጠይቀው ነበር:: ሰውየውም እንዲህ ሲል እንደመለሰላቸው ሀጂ በሽር ሲገልፁ:- «ፊታቸውን ኩምትር፤ ጭምድድ አደረጉና ሌባ ጣታቸውን ቀስረው አፍንጫቸውና አፋቸው ላይ አድርገው ኡስ! ኡስ! ብለው፤ ከኔ ሌላ ሰው አደራ እንዳይሰማህ አሉኝ:: ደንገጥ ብዬ ምነው? አልኳቸው:: እሳቸውም ከቀይ ባህር ጀምሮ በወሎና በመንዝ ተራራ ስር አልፎ እስከ ኬኒያ ባለው ምድረ በዳና ሜዳ ላይ የሰፈረው ህዝብ እስላም መሆኑን አታውቅም?... ተምረው ቢሰለጥኑ እና አንድ ቢሆኑ በአከባቢያቸው ካለው አረብና እስላም አገሮች ጋር እየተገናኙ ኢትዮጵያዊ ለሆነው የክርስቲያን ህዝብ ከባድ የሆነ ችግር ይፈጥራሉና እንዲሁ ዘላን ሆነው እየተጋደሉ ይቆዩ የማለት ጥናት ተደርጎ ከነገስታቶች የተሰጠ የበላይ መመሪያ መሆኑን ጋዜጠኛ ሆነህ እንዴት አታውቅም አሉ:: ደንግጬ ከቢሮዋቸው ወጣሁ::» (አብደላ አብዱረህማን ኑር፤ የዓይን ምሥክር፤ ገጽ 11) ሲሉ አስረድተዋል::

እንግድህ ይህ ሁሉ አለፈና የጠቅላላውን ኢትዮጵያዊ ህዝብ መብት በእኩልነት የሚያስከብር ሕገ መንግስት ፀደቀ:: ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች በጋራ አጨበጨቡ :: ሙስሊሙም የትምህርትን እድል አገኘ:: ምንም ያልነበረው የሙስሊሙ ተማሪ ቁጥር ቀስ በቀስ ማንሰራራት ጀምረ:: ምንም እንኳን ሙስሊሙ ከሀገሪቱ ህዝብ ከግማሽ በላይ ቢሆንም በየዩኒቨርስቲ የትምህርት ደረጃ ያለው ተሳትፎ ከ10-14 በመቶ የበለጠ አይደለም:: የሙስሊም ሴቶች ቁጥር ደግሞ ከሙስሊሙ ተማሪ ቁጥር 10% ቢሆን ነው:: ይህንን ቁጥር ለማሳደግ ልዩ ስራ መሠራት ነበረበት:: በሙስሊሙ ወላጅ ጥረት ነገሮች እንዲቀየሩ የገባው ወገን ደፋ ቀና ማለት ጀመረ::

ሙስሊም ተማሪዎች እስከ ዛሬ በጀመዓ (በጋራ) በዩኒቨርሲቲ ሀይማኖታዊ ግዴታቸውን ሲወጡ ከርመው አሁን መቀሌ ዩኒቨርሲቲ የወሰደው እርምጃ ምን የሚሉት ነው? ለሙስሊሞች ህይወት ያለ ሰላት ማለት ሕይወት ያለ እስትንፋስ እንደ ማለት ነው:: ለምን ቢሉ እንኳን ሠላም በሆነው ሀገር ይቅርና በጦርነት አውድማ እንኳ በጋራ (ጀመዓ) መስገድን ቁርዓን ደንግጓል:: ታዲያ አምና ይህንን ሰላትን የመከልከል እርምጃ የወሰደው አክሱም ዩኒቨርሲቲና አሁን የተከተለው መቀሌ ከጦርነት ቀጠና በላይ የከፋ ነው ማለት ነውን? ይህስ እርምጃ መቻቻል የሚያመጣ፣ ሙስሊሞች በሀገራቸውና በመንግስታቸው ላይ እምነት እንዲኖራቸው የሚያግዝ እርምጃ ወይንስ የሚገዘግዝ? ማንኛውም ሰው ሐይማኖቱን በግልም ይሁን በቡድን መተግበርን ማንም የማይሸራርፍበት መብቱ መሆኑን የኢትዮጵያ ህገመንግስት ደንግጓል:: ታዲያ ሕገ መንግስቱ በዩኒቨርሲቲው አይሰራም ማለት ነውን? የአሁኑስ እርምጃ ዓላማው ምንድነው? ምንስ ተፈለገበት? መንግስት ከጎረቤት ሀገር ኤርትራ ጋር የጦርነት ዝግጅት እየተጧጧፈ እንደሆነ አንዳንድ ሚዲያዎች እየዘገቡ ባሉበት፣ «ኤች አር 2003 የተባለ የኢትዮጵያ የዲሞክራሲና ተጠያቂነት» የተባለ አዋጅ በአሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ እንዳይፅድቅ መንግስት በወር በ50 ሺ ዶላር ጠበቃ ገዝቶ እየተሟገተ ባለበት ወቅት፤ በሱማሌ ክልል «ኦብነግ» ከተባለው ቡድን ጋር መንግስት ጦርነት ውስጥ በገባበትና በጎረቤት ሀገር ሱማሊያም የኢትዮጵያ መንግስት ሰላም አስከብራለሁ ብሎ ስቃይ እያየ ባለበት ሁኔታ ከሀገር ውስጥ ሙስሊሙን ፀረ-መንግስት አቋም እንዲኖረው የሚጋብዝ፣ በሀገሩ እንዲያፍር የሚያደርገው፣ ሙስሊሙ እንዳይማር ይታገል ከነበረው ከአፄ ሐይለ ስላሴ መንግስት ጋር መንግስትን የሚያመሳስለው አዋጅ ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ መደመጡ ይህ የሰላም ፈላጊ አካል ድርጊት ነውን? ነገሩ እንዴት ነው? ሠላምና መረጋጋት ለኢትዮጵያ አያስፈልጋትምን?

ዩኒቨርሲቲ የሀገሪቱን ተማሪዎች ተቀብሎ በበቂ ዕውቀት አንፂቸው ለሀገሪቱ የጀርባ አጥንት ማፍራት ነው ዓለማው:: ይህንንም ዓለማ ለማሳካት ተማሪዎች ከወላጆቻቸው ተለይተው በዩኒቨርሲቲ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት ቆይታ ያደርጋሉ:: ይህ ሲሆን ከህብረተሰቡ የወጡና የህብረተሰቡ አካል እንደመሆናቸው የህዝቡ መሠረታዊ ፍላጎቶችም ሁሉ የነርሱም ፍላጎቶች ናቸው:: ትምህርት ሊማሩ ወደ ዩኒቨርሲቲ ተላኩ እንጂ  ምነታቸውን ወደ ሚረሱበትና ወደ ማይተገብሩበት ካምፕ አልተላኩም:: አልያም አንዳች ኢስላማዊ ተግባራት የማይተገብሩበት ገዳም አይደለም ዩኒቨርሲቲ:: የኢትዮጵያ ህዝብ በሚከፍለው ግብር የተቋቋመው ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ከቤተሰባቸው ተቀብሎ ሊያስተምር እና ብቁ ዜጋ ሊያደርግ ተቋቋመ እንጂ ሰላትን ሙስሊሞች እንዲረሱትና እንዳይተገብሩት ብሎም ሐይማኖታቸውን ህግጋት እንዲጥሱ ከዚያም ከናካተው እንዲተው ሊያደርግ የተቋቋመ ተቋም አይደለም:: ሊሆንም አይገባም! ታዲያ መቀሌ ዩኒቨርሲ ሆይ ከትምህርታቸው ወይ ከሐይማኖታችሁ

አንዱን ምረጡ ማለቱ ምን ማለት ነው? ይህንን እያሉና እየወሰኑ ያሉ አካላት ሁሉ ምን እያደረጉ እንደሆነ አልተረዱትምን? «ሙስሊም ሆናችሁ ልትማሩ አትችሉም!» እያሉንስ አይደለ? አሁን ነው ጨዋታው አለ ሰውየው:: የሐይማኖት ነጻነት ይህ ነው? ለካስ ይህ ነው መቻቻል? የዓለም ተምሳሌት ያደረገን? እስቲ መላ በሉ? ሙስሊሙ ሐይማኖቱን ጠባቂ፤ ሀቀኛና መልካም ምግባረ ያለው ቢሆን ምንድ ነው ችግሩ? ምን አይነት ሙስሊም ተማሪ ነው የተፈለገው?

በሕገመንግስቱ አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ሀይማኖትን በግልም ሆነ በቡድን መተግበር እንደሚቻል በማያሻማ ቋንቋ ተቀምጦ ነበር:: ታዲያ የምሁራን ማዕከል የሆነው ዩኒቨርሲቲ ምን ነካው? እነርሱ ካልተገበሩ ማንስ ይተግብር? ሕገመንግስቱ በአንቀፅ 27 ንዑስ 3 ላይ ማንም በሌላ አካል ጫና ሀይማኖታዊ ተግባሩን ሊገታ እንደማይችል ቁልጭ ብሎ ተቀምጧል:: ታዲያ ለምንስ ከሐይማኖት አልያም ትምህርታችሁ አንዱን ምረጡ ተባሉ? ይህ አባባላቸው በእውነቱ የነፍጠኛው መንግስት ስርዓት ጋር ለውጥ አለውን? ለምን ቢሉ ትናንት አፄ ዮሐንስ በ1888 በሙስሊሞች ላይ «ስላም የሆንክ ሁሉ ክርስትና ተነስተህ ተጠመቅ:: አልያም ሀገሬን ኢትዮጵያን እንድትለቅ!» ሲል ያወጣውን አዋጅ ያስታውሰናል:: «ከትምህርታችሁ ወይ ከሀይማኖታችሁ አንዱን ምረጡ:: በጋራ እንስገድ ካላችሁ ዩኒቨርሲቲውን ለቃችሁ ውጡልኝ!» አይደል የአሁኑስ አባባል? ታዲያ ምን ለየው? በእውነት ዮሐንስ ተመልሶ መጣ እንዴ ያስብላል::

የመንግስት ተቋማት (የት/ት ተቋማትን ጨምሮ) ከሐይማኖት ነፃ (ሴኩላር) ይሁኑ ማለት ሁሉም በዚያ ተቋም የሚጠቀም ሁሉ ሀይማኖት አልባ ይሁን ማለት ነውን? እምነታችሁን ደጃፍ ጥላችሁ ግቡ ማለት ነውን? እንደነዚህ አካላት ትምህርት ተቋማቱ ከሐይማኖት ነጻ መሆን ስላለበት ሙስሊሞች ከኢስላም መሠረቶች አንዱ የሆነውን ሰላትን ሀይማኖቱ በሚያዘው መሠረት አይተግብሩ ማለት ነውን? የመንግስት ተቋማት ከሐይማኖት ነፃ ይሁኑ ማለት ምንማለት ነው? ቅን ልቦና ላለው ይህን መረዳት አያዳግትም:: ምክንያቱም በስርዓቱ ላይ ከቁርአን አልያም ከመፅሐፍ ቅዱስ አልያም ከሌላ የእምነት መፃሕፍት ተጽዕኖ ነፃ ይሁን ማለት እንደሆነ ህጉን ላነበበ ሁሉ ግልፅ ነውና:: በተቃራኒው እነዚህ ህጉን እንዳሰኛቸው የሚተረጉሙት አካላት ቢሮ በአጋጣሚ ጎራ ቢሉ «ይቅርታ እኔ ቢሮ መስሎኝ እንጂ ቤተክርስቲያን አልመሰለኝም ነበር::» ሊሉ ሁሳ ይችላሉ:: እንዴት ብለው እንዳማይጠይቁኝ ተስፋ አደርጋለሁ:: ምክንያቱም እርሶም በአንድ አጋጣሚ ወደ አንድ መንግስታዊ ቢሮ ቢሄዱ በቀላሉ ታዝበው ይሆናል:: የማርያምን፤ የኢየሱስን፤ የራጉኤል፤ የጊዮርጊስን ምስሎች፤ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ቢሮውን አጣበዋል:: አርተፊሻል ትንሽዬ የገና ዛፍ ከነሙሉ መብራቱ ጥግ ይዞ ቆሟል:: የፃሐፊያቸውም ሆነ የአለቃው ኮምፒዩተር ላፍታም ቢሆን መዝሙር ከማስደመጥ አይቦዝኑም:: በቃ ታቦት ብቻ ነው የቀረው እንጂ ቤተክርስቲያን ሆኗል:: ሕገ መንግስቱ ይህንን ነበር የሚከለክለው :: ሕጉንስ እውን ማን ጣሰ? ለምንስ መረዳት ተሳናቸው? ወይንስ አይፈልጉም? ሰዎቹ የማንን ሥራ ለመሥራት ወንበር ያዙ? ቢሮውስ የመንግስት ወይንስ የቤተክርስቲያን? ታዲያ ምነው ሙስሊሙ የመንግሥት ቢሮ ለሰላት አለዋለ?

ሰላት ሲሰገድ ደማቸው የሚፈላ አካላት አሉ:: አንዳንዶቹ የስልጣን አጋጣሚ በመጠቀም ህጉን አዛብተው ሊያሳምኑ ይዳዳቸዋል:: አያሌ ምክንያት ተብዬዎችን ይፈበርካሉ:: አንዳንዶቹ በትምህርት ተቋማት ውስጥ መስገድ ሁከት መፍጠር ነው ይሉናል:: ሰላትን በጋራ መስገድ ሁከት መፍጠር ሆነ? ይህማ ከሆነ መስጊዶች ሁሉ ይታገዱዋ? ምክንያቱም እንደነዚህ ሰዎች አመለካከት ሁኩት  የፈጠሩ

ናቸውና! ግለሰቦች ሕግን እያስታከኩ የራሳቸውን አጀንዳ ሲያስፈፅሙና ሙስሊሙን ከትምህርት የማራቅ ድብቅ ሴራ ሲዘረጉ መንግስትስ ዝም ብሎ እንዳልሰማ መሆን አለበትን? ወይንስ በግለሰቦች እያመካኘ ራሱ ነው እንዲህ የሚያደርገው? አንድ ህግ ማውጣት ቢያስፈልግ አልያም አንድ ደንብ ሲረቀቅ ሕዝቡ ይፈልገዋል አይፈልገውም? ይጠቅመናል ወይንስ አይጠቅመንም? ተብሎ ህዝቡ መክሮበት፣ አውቆት መሆን የለበትምን? አዲስ መስመር ተማሪው ቤተሰቡ ጋር ሲሆን አምስቱን የሰላት ወቅቶች በመስጂድ ይሰግድ ነበር። ወደ ዩኒቨርሲቲ ከገባ በኋላ ዩኒቨርሲቲው ለተማሪው ቤቱ፣ ሰፈሩና ሁሉም ነገሩ ነውና ሰላትም ሊሰግድ ግድ ይላል።

አንዳንዴ «ለምን ወደ አቅራቢያው መስጂድ ሄዶ አይሰግዱም።» ሲሉ ጥያቄ የሚያነሱ አካላት አልጠፉም። በቅንነት ብናስተውል አብዛኛው ዩኒቨርሲቲዎች ከከተማ ራቅ ብለው ነው የተሠሩት። ለምሳሌ ብናይ በአክሱም ዩኒቨርሲቲ ያሉ ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲው ውጭ ሄደው ለመስገድ ቢፈልጉ እንኳን እነርሱ ቀርተው የአክሱም ሙስሊም መች መስጂድ የመስራት ሕገ መንግሥታዊ መብቱ ተከበረለትና? ህገመንግስቱ አክሱም አልደረሰም እስኪባል ድረስ የማይሞከር ሆኗል። መቀሌ፣ አለማያ፣ አርባምንጭ፣ ዲላ፣ ወንዶ ገነት የመሳሰሉት ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ ከከተማው ከ5-8 ኪሎ ሜትር ርቀው ነው የሚገኙት። በዚያ የሚማሩ ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲው በቀን አምስት ጊዜ ለሰላት ወደ ከተማ ሊጓዙ ነው ማለት ነው። እንደው በትንሹ 5 ኪ.ሜ ቢገዝ እንኳን በቀን ለ50 ኪ.ሜ (ደርሶመልስ) ይጓዛል ማለት ነው። ተማሪው ይህንን ሊያደርግ ይችላል? ትራንስፖርት ኖሮ ቢሳካለት እንኳን ምኑን ተማረ? ይህ ሁሉ ማገናዘብ የሚችለው ዩኒቨርሲቲ ግን የራሳችሁ ጉዳይ አይነት ውሳኔ እየወሰነ ነው። በተቃራኒው በከተማ መሐል ያለውን ዩኒቨርሲቲ አዲስ አበባን ብናይ ዋና ዋናዎቹ ግቢዎች ያሉበትን ክፍለ ከተማን ብናይ 13 ቤተክርስቲያኖች ሲኖሩበት አንድም መስጂድ የለም። ይህንንም በመረዳት ነው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መስገጃ ሥፍራ ለተማሪው የሰጠው። ይህንን ሁሉ የሚያውቁት የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ግን ልክ የራሳቸው ተቋም እንደሆነ እያዘዙበት ነው። ዩኒቨርሲቲው የሚንቀሳቀሰው የሙስሊም ተማሪዎች ወላጆች በሚከፍሉት ግብር እንጂ በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት የግልን ወጪ አለመሆኑን እንዴት ዘነጉት? ወይንስ ምን ታመጣላችሁ ነውን?

እነዚህ የሙስሊሙን የመማርም ሙስሊም የመሆኑንም መብትን ጥያቄ ውስጥ መክተት የሚሹት አካላት «እኛ ሁሉንም ነው የከለከልነው እንጂ ሙስሊሙን ብቻ አይደለም።» በማለት ፍትሀዊ ለመምሰል ይሞክራሉ። ይህ ትክክለኛ የሚመስለው ምክንያት ለሙስሊሞች እንደታለመ የአደባባይ ሚስጢር ነው። በቀን አምስት ጊዜ በጋራ መስገድ ግዴታ የሆነባቸውን ሙስሊሞችንና ተመሳሳይ ተግባር የመፈፀም ግዴታ የሌለባቸውን የሌላ እምነት ተከታዮችን በእኩል መመልከት አግባብ ነውን? ለምሳሌ ድመትንና በግን በእኩል ሥጋ መብላት ብንከለክላቸው ማን ነው የሚጎዳው? በጉ መጀመሪያውኑ ሥጋ አይበላም። የአገዳው አዋጅ ቢነገርም ባይነገርም ለርሱ ለውጥ የለውም። ታዲያ ይህ አገዳ ድመቲቱን ለመከልከል የታለመ አይደለምን? ሶላትን በጀመዓ (በጋራ) መሥገድ ህገ-ወጥነት ነው ይለናል መቀሌ ዩኒቨርሲቲ። ይህ ሕገወጥነት ከሆነ ምንስ ህጋዊነት ሊኖር ይሆን? በሕገመንግስቱ የፀደቀው የሐይማኖት ነፃነት እንዲህ ሲናድ ማየት ምንኛ ይሰማል? የምሁራን ማፍለቂያው ህጉን ከናደ ኢትዮጵያን ምን ይበጃት ይሆን? ምንስ መላ አላት?

በኢስላም ከሰላት በላይ ምን አለ? ይህ የሰላትና የሂጃብ ጉዳይ መች ይሆን በማያዳግም መልኩ እልባት የሚገኝለት? የሙስሊሙ ተወካይ ተብዬው መጅሊስስ ምን እያደረገ ይሆን? ይህን እርምጃ ደገፈው ወይንስ ተቃወመ? አቋሙን ግልፅ ቢያደርግስ? ወደ አወንታዊውም ሆነ አሉታዊ አቅጣጫ የሚያደርገውን ብናውቅስ? ዝምታ ከመተባበር ተለይቶ ስለማይታይ ማለቴ ነው! ሙስሊሞች ሆይ! እኔን ጨነቀኝ ምን ይበጀን ይሆን? መላው ምን ይሆን? ከሰላት በላይ ምን አለንና? ያለችንና የቀረችን ዒባዳን እርሷኑ ልንከለከል? በኢስላማዊ አኳኋን በጋራ አትስገዱ ማለትን እምነታችሁን ጥላችሁ እኛን ምሰሉ የሚል ተልዕኮን ካነገበ የግልጽ ጦርነት ለኔ ለይቼ አላየውም:: እናንተስ?

እኔ የምለው በትምህርት ተቋማት ውስጥ ቁልፍ ቦታ ላይ የተቆናጠጡት ወገኖች ለትምህርት ወደ ውጭ ሲሄዱ ለምን በውጭ ያለውን ጥሩ ልምድ ተምረው አልተመለሱም? በየዩኒቨርሲቲው ሰላት በጋራ አይሰገድ የሚለው የ21ኛው ክፍለ ዘመን እሳቤ አይደለም:: ለምሳሌ በአሜሪካ፣ ካናዳ፣ ጀርመን፣ ኖርዌይ፣ እንግሊዝ፣ ግብፅ፣ ኬኒያ፣ ኒጀር፣ ታንዛኒያ ወዘተ በየዩኒቨርሲቲው በዩኒቨርሲቲው የተሠራ መስጂድ አለ:: ተማሪውም በነፃነት ነው ጀመዓም ሆነ ጁመዓ የሚሰግድበት:: ሌለው ቢቀር በ6ኪሎ ያለውን መስጊድ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ያውቀው የለ? ታዲያ ለምን ይህ ሁሉ ጉዞ?

የኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 27 ንዑስ 5 ላይ በግልፅ የአንድ ሀይማኖት የቡድን ተግባራት ሊታገድ የሚችልበት ሁኔ  ምን እንደሚመስል ተቀምጧል:: በሀገር ደህንነት፤ ጤና፤ ትምህርት እና ግብረ ገብ ላይ አደገኛ ሁኔታ ሆኖ ሲገኝ ሊታገድ እንደሚችል ተገልፃል::  ሶላትን በጋራ መስገድ ምን አደገኛ ነገር ፈጠረ? ተማሪው በማይክራፎን አይጠቀም? የትኛው ህዝብስ ላይ አደጋ አደረሰ? ማንስ የትድረስ አቤት አለ? በእግር ኳስ ሜዳ ወዘተ መስገድስ ለትምህርት ምን አደገኛ ችግር ፈጠረ? ትምህርት ላይ አደገኛ አዋጅ የሚያሳውጅ ደረጃ እስኪ ደርስ ሙስሊሙ ተማሪ አደገኛናነቱን አልተረዳም ማለት ነውን? ከግማሽ በላይ የሆነው የኢትዮጵያ ሙስሊም ከህዝቡ አካል አይደለምን? የትኛው ህዝብ አቤት አለ?  በህግ አስታኮ የራስን ጥላቻ ማሳየት ከሆነ አላማው እውን ይህ መቻቻል እንዲመጣ የሚያደርግ እርምጃ ነው ወይንስ የሚገዘግዝ?

የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤት ከሆነው ሙስሊም ህብረተሰብ ጋር ሳይወያዩ ከመጅሊስ ጋር በመሞዳሞድ ኢስላም ላይ አደጋ መፍጠር ምን የሚሉት ጫወታ ነው? ማንስ ማን እንደሆነ የማይታወቅ ይመስላችኋልን? መጅሊስ እንኳን ሙስሊሙን ሊወክል ይቅርና ራሱንም የሚወክል አይመስለኝም:: በተግባር እስከ ዛሬ አላየንምና:: ወይንስ ምን ይመጣል ነው? ቢፈልግ የሙስሊሙና የመንግስት ግንኙነት እንጠረጦስ ይውረድ «ምን ልታመጡ?» ማለት ይሆን? ህገ መንስግስቱ እንኳን የሀይማኖት ነፃነትን አረጋግጦ ይቅርና ቢገድብስ ሰላት በጀመዓ መስገድ ይቀራልን? ህገ መንግሰቱን ያረቀቁትና ያፀደቁት የሕዝቡ ወኪሎች እንጂ አምላክ አይደሉም:: ከግማሽ በላይ ከሆነው ከኢትዮጵያ ሙስሊም መብትና ፍላጎት ጋር የማይሄድ ከሆነ የግድ በሕዝቡ ወኪሎች እንደገና በህጋዊው መንገድ መስተካከል ይኖርበት ነበር:: ይህን በሕዝቡ ወኪሎች አማካኝነት የኢትዮጵያ ህዝብ ያፀደቀውን ሕገ መንግስት የምሁራን ማፈሪያ የሆነው ዩኒቨርሲቲ ከጣሰው ኢትዮጵያ ምን መላ አላት? መንግስት ማለት የህዝብ አገልጋይ አይደለምን? ከሆነስ ህዝብ እንደመረጠው መብቱን ሊያሰከብር ካልቻለ አሁንም ህዝቡ ጥሩ አገልጋይ መምረጥ መብቱስ አይደል? እኔስ በግሌ «ለሙስሊሙ ኢህአዴግ ይሻላል፣ ምረጡ፣ ለሀይማኖት ነፃነት ይበጀናል:: ወዘተ»  እንደ እስከዛሬው የምልበት አፍም የለኝ:: ብልስ ማን ይሰማኛል? የመጨረሻው መልዕክቴ:- የሙስሊም መሪዎች ዛሬ በሙስሊሙ ላይ

ለደረሰውና ለሚደርሰው ተጠያቂነታችሁን ላፍታም ቢሆን እንዳትረሱ፡፡ እያንዳንዱ ሙስሊምም እንዲሁ፡፡ እንዲህ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ ግንባር ቀደም ተዋናኝ መሆን የነበረበት መስማት ባይፈልግም መጅሊስ ነው፡፡ ለምን ቢሉ? ወከልኳችሁ ብሎናልና! ይህንን መሰል የመብት ረገጣን ለማስቀልበስ ካልተሯሯጡ ምኑ ላይ ነው ውክልናቸው? አረ አይቀሬ ለሆነው አኪራ ስንል ዝምታን እንምረጥ! እናንተ መሪዎች ሆይ! አላህን እንፍራ!

ለዛሬ አይበቃኝም? እኔ ራሴን ወክዬ ይህን ያህል አልሁ፡፡ በቃኝ፡፡ ተራው እና መድረኩ አሁን የእናንተ ነው። ተጠቀሙበት። በዱዓም እንተዋወስ! ወሰላሙአለይኩም!